የሞንጎመሪ ካውንቲ አጠቃላይ የጎርፍ አስተዳደር እቅድ

የጎርፍ አስተዳደር እቅድ ለምን አስፈለገ?

በሞንትጎመሪ ካውንቲ በሕዝብ እና በግል ንብረት ላይ አደጋ የሚፈጥሩ የጎርፍ መጥለቅለቅ ክስተቶች እየጨመሩ መጥተዋል። ለእነዚህ ክስተቶች መጨመር የተለያዩ ምክንያቶች ቢኖሩም በዋንኛነት የሚጠቀሱት በልማት ምክንያት ፍሳሽ የማያሳልፉ ወለሎች መበራከት እና ከፍተኛ የዝናብ መጠን መጨመር ዋና ዋናዎቹ ናቸው። እነዚህ ተፅእኖዎች ቀጣይነት ባለው የእድገት እና የአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት ይጨምራሉ ተብሎ ይጠበቃል።

የጎርፍ አስተዳደር እቅድ ምንድን ነው?

የሞንጎመሪ ካውንቲ የአካባቢ ጥበቃ ዲፓርትመንት (DEP) አጠቃላይ የጎርፍ አስተዳደር ዕቅድ በማዘጋጀት ላይ ነው። የጎርፍ አስተዳደር እቅድ ይህንን እያደረገ ያለውን አደጋ ለማሳወቅ እና በመጨረሻም ካውንቲው ችግሩን ለመፍታት የሚያስችለውን መረጃ የሚያዳብርባቸውን መንገዶች ይዘረዝራል። ይህ እቅድ በሚቀጥሉት ጥቂት አመታት ውስጥ በርካታ የስራ ደረጃዎችን ያካተተ ሲሆን ፤ የተጋላጭነት ምዘናዎችን፣ ዝርዝር ስለጎርፍ ጥናቶችን፣ የመከላከያ ዲዛይኖችን እና የማስተካከያ ፕሮጀክቶችን እና የፕሮግራም ምላሾች ትግበራን ያካትታል።

የዳሰሳ ጥናቱን ይሙሉ

ይህንን ሂደት ለመጀመር ፣ ከእርስዎ መስማት እንፈልጋለን! በጎርፍ አደጋ የት ፣ መቼ እና እንዴት ጉዳት እንደደረሰብዎ ለማወቅ እንፈልጋለን። ይህን የመረጃ ስብስብ በሁሉም የካውንቲው ክፍሎች ከሚኖሩ ነዋሪዎች በሚገኝ መረጃ ማደራጀት ፣ የጎርፍ አካባቢዎችን፣ መጠንን እና አይነትን ለመረዳት ወሳኝ ይሆናል። ሁሉም መልሶች ሚስጥራዊ ሆነው ይቆያሉ።

የዳሰሳ ጥናቱን ለማጠናቀቅ የኪውአር ኮዱን (QR code) ስካን ያድርጉ ወይም ከታች ያለውን ሊንክ ይጠቀሙ።

https://bit.ly/MocoFloodSurvey

DEPARTMENT OF ENVIRONMENTAL PROTECTION
MONTGOMERY COUNTY • MARYLAND



ለጎርፍ መጥለቅለቅ ምክኒያቶች ምንድናቸው?

በካውንቲው ውስጥ የጎርፍ መጥለቅለቅ ሊከሰት የሚችለው የአካባቢው የዝናብ ፍሳሽ መጠን ከአካባቢው የአውሎ ንፋስ ፍሳሽ ስርዓት አቅም በላይ ሲሆን ወይም ወደ መሬት ውስጥ ሰርጎ መግባት ባለመቻሉ ነው። ይህ ፕሉቪያል (Pluvial) ጎርፍ ይባላል፣ በሌላ መልኩ "የከተማ ጎርፍ" ወይም "ሎት ቱ ሎት / lot to lot) ጎርፍ" በመባል ይታወቃል። የጎርፍ መጥለቅለቅ በጅረቶች ወይም በወንዞች ከመጠን በላይ በመሙላት ምክንያት ሊከሰት ይችላል። የዚህ አይነት ጎርፍ የወንዞች ጎርፍ በመባል ይታወቃል። በእነዚህ በሁለቱም ምክኒያት የሚመጡ አደጋዎች ከሕይወት አስጊ እስከ አስጨናቂ ተጽእኖዎች ሊያደርሱ ይችላሉ።

ወቅታዊ መረጃ ያግኙ

ስለ ፕሮጀክቱ የበለጠ ለማወቅ እና ስለቀጣይ ፕሮግራሞች ወቅታዊ መረጃ ለማግኘት የፕሮጀክቱን ድህረ-ገጽ ይጎብኙ!

www.montgomerycountymd.gov/flooding

DEPARTMENT OF ENVIRONMENTAL PROTECTION
MONTGOMERY COUNTY • MARYLAND